# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የአዲስ አመት ማዜማ**

የአዲስ አመት ዋዜማን December 31 ከ 5 p.m. ጀምሮ እናከብራለን። ምግብ ይኖረናል፣ የጸሎትና የአምልኮ ጊዜ ይኖረናል፤ ቲሸርት ይዘጋጃል፤ የስነ-ጽሐፍ ጊዜ ይኖረናል። ስነ-ጽሑፍ ለማቅረብ የምትፈልጉ ለረድኤቱ አስታውቁ። ሰዎችን ጋብዙ። ጌታ ይባርካችሁ።

**የአገልግሎት ጥሪ**

በተለያየ መስክ ለማገልግለ የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን አነጋግሩ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ።

**እርስ በርስ እንተያይ**

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

“ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡ 30-31)



⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




“ያስተምራቸውም ዘንድ መልካሙን መንፈስህን ሰጠሃቸው።”
(ነህ. 9:20)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**November 10, 2019** | **ጥቅምት 30፣ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| **ጸሎት** .......................... | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| **አምልኮ**........................ | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| **ፕሮግራም መሪ** ............ | ወንድም ተረፈ አንሼቦ |
| **ቃል** ............................ | እህት ሰናይት ከበደ |
| **ማጠቃለያ** .................... | ወንድም ተረፈ አንሼቦ |

## የሳምንቱ ጥቅስ

"በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" (2ጴጥ. 1:20-21)፡፡

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አሰፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ሲሳይ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| አያሌው/ጸደቀ | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### መንፈስ ቅዱስ አስተማሪው መንፈስ

*"አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል.. " (ዮሐ. 14፡ 25-26)፡፡*

መንፈስ ቅዱስ በኛ ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል አንዱ ቃሉን ማስተማር ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ የቃሉን ፍቺ ለአማኞች ያበራል፡፡ ጌታችን ከላይ በሰፈረው ክፍል ይንንኑ አስተምሮናል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ሐዋሪያው ዮሐንስ ሲጽፍ "እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ" በማለት ይመክረናል (1ዮሐ. 2:27)፡፡ እንዲሁም በብሉይ ኪዳን "ያስተምራቸውም ዘንድ መልካሙን መንፈስህን ሰጠሃቸው" (ነህ. 9:20) ተብሎ የመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት ተገልጿል፡፡ ከቃሉ እንደምንማረው መንፈስ ቅዱስ የቃሉ መምህር ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ሲስያስተምር በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለውን የቃሉን ሃሳብ ያበራልናል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ነጂነት ነው የተጻፈው፡፡ ሐዋሪያው ጴጥሮስ እንዳስተማረን "በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" (2ጴጥ. 1:20-21) ፡፡ ክፍሉ የሚናገረው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ደራሲ (ቃሉን ወደ እኛ) ያመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንንም ቃል ሊተረጉምልንና ሊያስተምረን የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ መቼም አንድ እውነት አለ፡ ጽሑፍ ሁሉ የሚገልጸው በደራሲው ውስጥ ያለውን ሃሳብ ነው፡፡ ሲተረጎምም እንዲሁ በደራሲው ውስጥ ያለውን ሃሳብ ከማግኘት አንጻር ነው መተርጎም ያለበት፡፡ በአለም ስርዓት ያሉ ሕጎች እንኳ ሲተረጎሙ የህግ አውጪው ሃሳብ ምንድን ነው ተብሎ ይጠየቃል፡፡ ሕጉም ያንን ሃሳብ በሚያጸና መልኩ ይተረጎማል፡፡ የግዚአብሔር ቃል ደግሞ የሚገልጽልን በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ ደግሞ ያለ መንፈስ ቅዱስ እገዛ ልንረዳው አንችልም፡፡ ስለዚህ ነው ቃሉ ይህንኑ ሲገልጽልን "መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው፡፡ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም፡፡ እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም" (1ቆሮ. 2:10-12) በማለት ያስተምረናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ያውቃል፡፡ ስለዚህም ቃሉን በመግለጽና በማስተማር ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል (ዮሐ. 16:13)፡፡

ወገኖቼ፡- እግዚአብሔር የሚገለጠው በቃሉ ውስጥ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ደግሞ የሚገልጥልንና የሚያስተምረን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ ቃሉን እንወቅ፤ ቃሉን ደግሞ ለማወቅ ወደ መንፈስ ቅዱስ እንቅረብ፡፡ የቃሉን ፍቺ ያበራልናል፡፡